2023
2024

የመከባበር መመሪያዎች

# የሃይማኖት ልዩነት

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
www.montgomeryschoolsmd.org

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

VISION

## ራእይ

ለእያንዳንዱና ለማንኛውም ተማሪ እጅግ የላቀውን ህዝባዊ ትምህርት በማቅረብ መማርን እናበረታታለን።

## ተልእኮ

እያንዳንዱ ተማሪ በኮሌጅ እና በሥራ መስክ ውጤታማ እንዲሆን/እንድትሆን፣ በአካደሚክስ፣ ችግር የመፍታት ዘዴ/ ብልሃት ፈጠራ፣ እና የማህበራዊ ስሜት ክህሎቶች ይኖሩታል/ ይኖሯታል።

## ዋና ዓላማ

ሁሉንም ተማሪዎች የወደፊት ህይወታቸው እንዲዳብር/ እንዲበለጽግ ማዘጋጀት፡፡

## ዋነኛ እሴቶች

መማር/እውቀት
ግንኙነቶች
አክብሮት
ልቀት
ፍትኃዊነት/ሚዛናዊነት


Board of Education የትምህርት ቦርድ

Ms. Karla Silvestre ሚ/ስ ካርላ ሲልቨስትሪ
PresidentፕሬዚደንትPresident ፕሬዚደንት

Mrs. Shebra L. Evans ወ/ሮ ሸብራ ኤል. ኢቫንስ
Vice President ም/ፕሬዚደንት

Ms. Lynne Harris ሚ/ስ ለይኔ ሃሪስ

Ms. Grace Rivera-Oven ሚ/ስ ግሬስ ሪቬራ-ኦቨን

Mrs. Rebecca K. Smondrowski ወ/ሮ ርብቃ ኬ. ስሞንድሮውስኪ

Ms. Brenda Wolff ሚ/ስ ብረንዳ ዎልፍ

Ms. Julie Yang ሚ/ስ ጁሊ ያንግ

Mr. Sami Saheed አቶ ሳሚ ሰዒድ
Student Member ተማሪ አባል

Montgomery County Public Schools (MCPS)
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
Administration አስተዳደር

Monifa B. McKnight, Ed.D. ሞኒፋ ቢ. ማክኒት ዶ/ር
Superintendent of Schools የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

Mr. M. Brian Hull ሚ/ር ኤም ብራያን ሃል
Chief Operating Officer ዋና ሥራ አስኪያጅ

Patrick K. Murphy, Ed.D. ፓትሪክ ኬ.መርፊ ዶ/ር
Deputy Superintendent ምክትል ሱፐርኢንተንደንት

Mr. Brian S. Stockton ሚስተር ብሪያን ኤስ ስቶክተን
Chief of Staff ዋና የሠራተኞች ሃላፊ

Mrs. Stephanie P. Williams ወይዘሮ ስቴፋኒ ፒ. ዊሊያምስ
General Counsel ጀነራል ካውንስል

Ms. Elba M. Garcia ሚስ ኤልባ ኤም ጋርሺያ
Senior Community Advisor የማህበረሰብ ከፍተኛ አማካሪ

Dr. Patricia E. Kapunan ዶክተር ፓትሪሺያ ኢ ካፑናን
School System Medical Officer የትምህርት ቤቶች የጤና መኮንን



850 Hungerford Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

የመከባበር መመሪያዎች

# የሃይማኖት ልዩነት

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
www.montgomeryschoolsmd.org

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

© ጁላይ 2023
Montgomery County Public Schools
Rockville, Maryland

Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

**OFFICE OF THE SUPERINTENDENT OF SCHOOLS**

ሴፕቴምበር 2023

ውድ ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና የሥራ ባልደረቦች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ማህበረሰባችን መገለጫ የሆነውን ደማቅ ብዝሃነት እውቅና በመስጠት እናከብራለን። በትምህርት ስርዓታችን ውስጥ እያንዳንዱ ግለሰብ እውነተኛ ተቀባይነት እንዳለው እና ምቾት እንዲሰማው ማረጋገጥ የኛ ጽኑ ቁርጠኝነት ነው። አካታች የሆነ አካባቢን በማበልፀግ ሁሉም ግለሰቦች በንቃት እንዲሳተፉ፣ እንዲያስተምሩ እና በከፍተኛ ደረጃ የሚማሩበትን መሰረት እናመቻቻለን።

ሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት እንደሚቀስሙ ለማረጋገጥ አንድ ላይ መረባረብ አስፈላጊ ነው። ለዚህ ዓላማ ያለን ቁርጠኝነት በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA ላይ ከአድሎአዊነት የፀዳ፣ ፍትሃዊነት እና የባህል ብቃትንየማስፈን እሳቤ ውስጥ የተካተተ ነው። መድልዎ፣ ጉልበተኝነት እና ትንኮሳ በት/ቤቶቻችን ውስጥ ቦታ የላቸውም፣ ስለሆነም ለእያንዳንዱ ተማሪ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አወንታዊ እና ምቹ የሆነ የመማሪያ አካባቢዎችን ለመፍጠር በቁርጠኝነት እንቆማለን። የጥላቻና አድሎአዊነት ድርጊቶች እየጨመሩ በመጡበት ወቅት፣ እያንዳንዱ ተማሪ አስፈላጊ መሆኑን ልናረጋግጥ እና ተማሪዎቻችን እምነታቸውን በተግባር በነጻነት የመግለጽ መብታቸውን ማስከበር አለብን።

ይህንን ቁርጠኝነት ለመፈጸም፣ በትምህርት ስርዓታችን ውስጥ ካለው የሀይማኖት ብዝሃነትና ልዩነት ጋር የተያያዙ ቁልፍ ፅንሰ ሀሳቦችን የሚያብራራ አጠቃላይ ሰነድ አዘጋጅተናል። ይህ ሰነድ የሚከተሉትን ጨምሮ አስፈላጊ ጉዳዮችን ያካትታል

መቅረት፡- ተማሪዎች በአካዳሚክ እድገታቸው ላይ ምንም ጉዳት በማያስከትል መልኩ እምነታቸውን መተግበር እንደሚችሉ በማረጋገጥ ሃይማኖታዊ በዓላትን ለማክበር መቅረትን በተመለከተ መተግበር ያለባቸው መመሪያዎች እና ሂደቶች።

ፀሎት እና ሃይማኖታዊ አለባበስ: ተማሪዎች ሃይማኖታዊ እምነቶቻቸውን በሥርዓት ለመተግበር የሚያስችላቸው የጸሎት እና የሃይማኖታዊ አለባበሶችን በተመለከተ ተፈጻሚነት ያላቸው ፖሊሲዎች እና መስተንግዶዎች።

ሃይማኖት በትምህርት ውስጥ በስርዓተ ትምህርታችን የትምህርት መገልገያ ቁሳቁሶች ውስጥ ስለ ሃይማኖት ማካተት፣ ስለ ተለያዩ እምነቶች ግንዛቤን ለማስጨበጥ እና አክብሮትን ለማጎልበት ተግባራዊ የሚደረጉ አቀራረቦች እና መመሪያዎች።

ምግብ እና የሃይማኖት በዓላት፡ ኃይማኖታዊ የአመጋገብ ገደቦችን ማክበር እና ሃይማኖታዊ ሥርዓቶችን ለማከናወን ተስማሚ የምግብ አማራጮችን ማቅረብ።

ከትምህርት-ሰአት-ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች፡- ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለሃይማኖታዊ ተግባራት ሁሉን ማቀፍ እና ሁሉም ተማሪዎች ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፉ በማድረግ በተገቢ ሁኔታ ማስተናገድ።

ለሁሉም ሰው የመከባበር ባህል ማዳበር፡- በት/ቤታችን ማህበረሰብ ውስጥ የሚገኙ የተለያየ ዳራ እና እምነቶች የመከባበር፣ የመተሳሰብ እና የማድነቅ ባህልን ለማዳበር የታለሙ ስልቶች እና ተነሳሽነቶች።

ይህ የተጠቃለለ ሰነድ የሀይማኖት ነፃነትን፣ አካታችነትን እና ለሁሉም ተማሪዎች የመከባበር መርኖችን ለመጠበቅ ያለንን ቀጣይ ቁርጠኝነታችንን ያረጋግጣል። እያንዳንዱ የትምህርት ቤቶቻችን ማህበረሰብ አባል ከሠነዱ ይዘት ጋር እንዲተዋወቁ እና እያንዳንዱ ተማሪ በአካዳሚክ፣ በማህበራዊ ስሜት እና በመንፈስ የሚያድግበትን ከባቢ ለማጎልበት እንዲተባበሩን እናሳስባለን።

ከመልካም ወዳጅነት ጋር

Monifa B. McKnight, Ed.D.
Superintendent of Schools
ሞኒፋ ቢ. ማክኒት ዶ/ር
የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

……………..

# ማውጫ


ፈጣን የማጣቀሻ መመሪያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . iii

መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሃይማኖት ልዩነትን ማክበር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

ሃይማኖታዊ በዓላትን ለማክበር መቅረት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2

አተንዳንስ እና ሃይማኖታዊ በዓላትን ለማክበር መቅረት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2

የሃይማኖታዊ በዓላትን ለማክበር ከቀሩ በኋላ የትምህርት ሥራን ማካካስ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2

ጸሎት እና ሃይማኖታዊ አለባበስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ጸሎት በትምህርት ቤት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ሃይማኖታዊ አለባበስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ሃይማኖት በማስተማር ፕሮግራም. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ሃይማኖት ከትምህርት ቤት በሚሰጡ ሥራዎች ላይ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

በሃይማኖታዊ ምክንያቶች ከትምህርት ፕሮግራሞች ለመቅረት ፈቃድ መጠየቅ . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

በትምህርት ቤቶች ውስጥ ስለ ሃይማኖት ወይም ሃይማኖታዊ በዓላት ማስተማር. . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

በት/ቤት ሃይማኖታዊ ስብሰባዎች እና ኮንሰርቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

ምግብ እና ሃይማኖት ማክበር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ የአመጋገብ ገደቦች እና ጾም . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

ሃይማኖታዊ የመረጃ ቁሳቁሶችን ማሰራጨት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለማሰራጨት ከተማሪ የሚቀርብ ጥያቄ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የተማሪ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች እና ክለቦች . . . . . . . . . 5

በሃይማኖታዊ ድርጅቶች ባለቤትነት የተያዙ መገልገያዎች ላይ የ MCPS አጠቃቀም . . . . . . . . . . . . 6

በት/ቤቶች እና በእምነት ማህበረሰቦች መካከል የሚደረግ ወዳጅነትና ትብብር . . . . . . . . . . . . . . . 6

ሁሉንም የመከባበር ባህል ማዳበር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 6

# ፈጣን መረጃ ለማግኘት የሚጠቅም መመሪያ
# የተማሪዎች መገልገያዎች/ሪሶርሶች

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ለድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመሮች
**24-ሰዓት መረጃ፣ ወደሚመለከተው ማስተላለፍ እና ጠቃሚ ውይይት**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማዕከል ለአስቸኳይ ጥሪ ክፍት የስልክ መስመር፡ Hotline/EveryMind/ . . . . . . 301-738-2255 እና https://www.every-mind.org/
በይነመረብ ላይ የሚያነጋግሩ ሰዎች ያሉበት እና የድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር፣ 24 ሰዓት የማወያየት አገልግሎት ይሰጣል።

Montgomery County Crisis Center - 240-777-4000
ሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማእከል
ቀውስ ማዕከል የአእምሮ ጤና ችግር ላጋጠማቸው ግለሰቦች 24/7 ነፃ የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል።

Youth Crisis Hotline of Montgomery County 301-738-9697
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ወጣቶች የድንገተኛ ጥሪ ስልክ መስመር
በሰለጠኑ ካውንስለሮች አማካይነት 24 ሰዓት በስልክ የማማከር ድጋፍ እና ሪፈራል የምስጢር አገልግሎት ይሰጣል።

## የደህንነትና የፀጥታ አስጊ ሁኔታዎችን ሪፖርት ለማድረግ፡-

MCPS ስርአት አቀፍ የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር ቢሮ: 240-740-3066
MCPS Office of Systemwide Emergency Management
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶችን እና ጽ/ቤቶችን ደህንነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው ቢሮ።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የተማሪ ደህንነት እና ህግ ማክበር፡- SWC@mcpsmd.org or TitleIX@mcpsmd.org . . . 240-740-3215
MCPS ዲስትሪክት አቀፍ Title IX አስተባባሪ እና ዲስትሪክት አቀፍ የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነት ግንኙነት። ስለ ተማሪ ደህንነት እና ደንብ ማክበር (SWC) በዚህ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፡- https://www.montgomeryschoolsmd.org/compliance/. SWC ከትምህርት ቤቶች፣ ከጀነራል ካውንስል ጽ/ቤት እና ከሌሎች MCPS ጽ/ቤቶች እና ከማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ እና መመሪያዎች፣ ከሰዎች ግንኙነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ከመተግበር አኳያ፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ (Title IX ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ)፣ እና ማስፈራራት፣ የሕፃናትን በደል እና ቸልተኝነት መገንዘብ እና ሪፖርት ማድረግ፣ ጥላቻና-አድሏዊነት፣ የጥላቻ እና የተማሪ የጾታ ማንነት ጉዳዮችን በሚመለከት ከላይ ከተጠቀሱት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ይሠራል።

MCPS Cyber Safety dropbox፡- . .CyberSafety@mcpsmd.org
MCPS ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ኦንላይን እንቅስቃሴን ሪፖርት ማድረጊያ Dropbox።

ከኮምፒተር ኔተዎርኮች ጋር ስለተገናኙ ጉዳዮች የጥቆማ መስመር - Cyber Tipline . . . . . . . . . . . . . . 1-800-843-5678
24/7 ልጆችን ለወሲብ ድርጊት በማባበል የተጠረጠሩትን ሪፖርት ለማድረግ የድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር፣ ከቤተሰቦቻቸው ውጪ የሚፈፀሙ ወሲባዊ ድርጊቶች፣የህፃናት ፖርኖግራፊ፣የህፃናት ወሲባዊ ቱሪዝም፣የህፃናት የወሲብ ንግድ፣ለልጆች የሚላኩ ያልተጠየቁ ጸያፍ ቁሶች፣የተሳሳተ/የተጭበረበሩ የተጠቃሚ ስሞች እና አሳሳች ቃላትን ወይም በኢንተርኔት ላይ የሚለጠፉ ዲጂታል ምስሎችን ሪፖርት ለማድረግ 24/7 የሚያገለግል የስልክ መስመር።

Safe Schools Maryland Hotline . . . . . .833-MD-B-Safe (833-632-7233)
ደህንነታቸው የተጠበቀ የሜሪላንድ ት/ቤቶች የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ የስልክ መስመር
24/7 ስም ሳይገለጽ ነፃ የሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት ለተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለት/ቤት ሰራተኞች፣ ለወላጆች እና ለጠቅላላው ማህበረሰብ የአእምሮ ጤና ጉዳዮችን ጨምሮ ማንኛውንም የት/ቤት ወይም የተማሪ ደህንነት ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ ያገለግላል። ስልክ የሚደውለውን ሰው ማንነት በመደበቅ ስለተፈጠረው ክስተት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ አግባብ ካላቸው ቢሮዎች ጋር መረጃ ይጋራል።

Montgomery County Child Protective Services, Department of Health and Human Services
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎት፣ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት
(24 ሠዓት ክፍት የስልክ መስመሮች) . 240-777-4417 ወይም 240-777-4815 TTY
ተጠርጣሪ የልጅ ጥቃትን ወይም ቸልተኝነትን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የልጆች ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት ክፍል ለማሳወቅ 24/7 ሪፖርት የሚቀበል የስልክ መስመር።

ለአደጋ ተጋላጭ ጎልማሶች የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጎልማሶች ጥበቃ አገልግሎት 240-777-3000፣ 240-777-4815 TTY
በአዋቂዎች ላይ የሚጠረጠር ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ለማድረግ 24/7 ክፍት የሆነ የስልክ መስመር።

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል (24 ሰዓት) ስልክ፡- 240-773-5400
በልጆችና በጎልማሶች ላይ የሚፈጸሙ የወሲብ ወንጀሎችን፣ የአካል ጉዳተኛ ልጆችን፣ ሸሽተው፣ የጠፉ ልጆች፣ ከባድ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ የተጋላጭ አረጋውያን ጥቃት/አደጋ በአዋቂዎች ላይ የሚደርስ በደል፣ እና የተመዘገበ ሪከርድ ያላቸው የወሲብ ጥቃት ወንጀለኞችን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ ለማሳወቅ 24/7 የስልክ መስመር።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ፡-
የአደንዛዥ ዕፅ እና የወሮበሎች (ጋንግ) የጥቆማ መስመር። 240-773-ወሮበላ (GANG (4264) ወይም 240-773-አደንዛዥ እፅ (DRUG) (3784)
በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ህገ-ወጥ እጽ ማዘዋወር/የወሮበሎች ቡድን (ጋንግ) እንቅስቃሴዎችን የሚመለከት ማንነት ሳይገለጽ ጥቆማ ለማቅረብ 24/7 ክፍት የስልክ መስመር።

## MCPS ሪሶርሶች

ካውንቲ አቀፍ የተማሪ አመራር
www.montgomeryschoolsmd.org/departments/student-leadership

ዳይሬክተር፣ የተማሪ አመራር እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች 240-740-4692

ተማሪ የቦርድ አባል
www.montgomeryschoolsmd.org/boe/members/student.aspx

የትምህርት ቦርድ ጽ/ቤት ስልክ፡- . . . . . . . . 240-740-3030

የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ቢሮ ዋና ኃላፊ . . 240-740-3100

ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት፣ ደህንነት፣ መማር እና ስኬት . .240-740-5630
ስለ ሰክሽን 504 ውሳኔ እና አፈጻጸም 240-740-3230

## የሞንትጎመሪ አስቸኳይ ላልሆኑ ጉዳዮች መገልገያዎች (ሪሶርሶች)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ አስቸኳይ ላልሆነ ጥሪ የስልክ መስመር
301-279-8000

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች የመረጃ መስመር
የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ አጠቃላይ መረጃን ያነጋግሩ 311, 301-251-4850 TTY
ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች ውጭ240-777-0311

## MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያዎች

በዚህ ድረ-ገጽ አማካይነት ከ MCPS ጋር ሁልጊዜ መገናኘት ይችላሉ፡- www.montgomeryschoolsmd.org
አጠቃላይ ተቋሙን የሚመለከት መረጃና የአስቸኳይ ሁኔታ ማስታወቂያዎችን ለማግኘት፡-

ትዊተር፡- MCPS on Twitter . . www.twitter.com/mcps
ትዊተር በስፓንሽኛ፡- MCPS en Español www.twitter.com/mcpsespanol

MCPS ፌስቡክ፡- www.facebook.com/mcpsmd
ፌስቡክ በስፓንሽኛ፡- MCPS en Español . www.facebook.com/mcpsespanol

የማንቃት/የማስጠንቀቅ መልክቶች፡- Alert MCPS . . . www.montgomeryschoolsmd.org/alertMCPS

988 SUICIDE & CRISIS LIFELINE

988 LÍNEA DE PREVENCIÓN DEL SUICIDIO Y CRISIS

## MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ክስተት ማስታወቂያዎች (የቀጠለ)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ፈጣን መልክቶች፣ ኢሜይል መልክቶች እና ዘገባዎች - MCPS QuickNotes Email Messages and Newsletter . www.mcpsQuickNotes.org

MCPS የመረጃ አገልግሎትን ይጠይቁ፡-

ስልክ . . . . . . . . . . . . . . . 240-740-3000
የስፓንሽኛ አስቸኳይ የስልክ መስመር. . . . . 240-740-2845
Email . . . . . . . . . . AskMCPS@mcpsmd.org

MCPS የማህበረሰብ መረጃ ቢሮ 240-740-2837

ቴሌቪዥን፡ MCPS Television . www.mcpsTV.org; Comcast 34, 998; RCN 89, 1058; Verizon 36

በድምፅ የተቀረጸ የአስቸኳይ ጊዜ እና የአየር ሁኔታ መረጃ . . . . . . . . . . . . 301-279-3673

## MCPS ሪሶርሶች የሚገኙበት ድረ-ገጽ
www.montgomeryschoolsmd.org

ዳሰሳ ወይም ቅኝት፡-

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ት/ቤቶች የመረጃዎች ዝርዝር ማውጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች የመረጃዎች ዝርዝር ማውጫ

MCPS ስልታዊ (ስትራቴጂያዊ) እቅድ

አትሌቲክስ

Be Well 365

የትምህርት ቦርድ
ጉልበተኝነት፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ ዛቻ/ማስፈራራት

የአውቶቡስ መስመሮች

የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነት

የኮሌጅ እና የሙያ ማዕከል

የግንዛቤ ትምህርት Common Sense Education

የኮርስ ጥንቅር መግለጫ

የማህበራዊ ሚዲያዎችንና ሌሎች የዲጅታል መሳሪያዎችን ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ መጠቀምና የኢንተርኔት ደህንነት - Cybercivility and CyberSafety

የዲፕሎማ መስፈርቶች

ወሮበሎች (ጋንግ) እና የወሮበሎች ተግባር

## MCPS የሪሶርስ ድረ-ገጽ (የቀጠለ)
www.montgomeryschoolsmd.org

የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ

የሃይማኖት ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች

ስለ ተማሪ ጾታዊ ማንነት መገለጫ መመሪያ

ምሣ የምግብ ዝርዝር

የሜሪላንድ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ምዘናዎች

ፀረ-መድሎ

በኦንላይን የመመረቂያ ፈለግ

የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት

መርኆች እና ደንቦች

የስነልቦና አገልግሎቶች

የተማሪ ሠራተኛ አገልግሎቶች

የልጅ መበደል እና ቸልተኝነት ሪፖርት ማደረግ

ፍትኃዊ ተሐድሶ

በት/ቤት የካውንስሊንግ እገልግሎቶች

የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች

የትምህርት ቤት ደህንነት

ፆታዊ ጥቃት

የማህበራዊ ሚድያ ዲጂታል ሲትዝንሽፕ
(Social Media Digital Citizenship)

ልዩ ትምህርት

ልዩ ፕሮግራሞች

ስልታዊ የእቅድ ዝግጅት

የተማሪ ስነ-ምግባር ደንብ

የተማሪ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ መማር - eLearning

የተማሪ የግል ገመና

የተማሪ አገልግሎት ትምህርት

ራስን መግደል መከላከል

የሰመር ትምህርት ቤት
Summer School

# መግቢያ

## በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የኃይማኖት ብዝሃነትን ማክበር

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለሁሉም ተማሪዎች ስኬታማ እና የበለፀጉ ዕድሎችን ለማበርከት ቁርጠኛ ነው የቁርጠኝነቱ አካል ተደርጎ መወሰድ ያለበት፥ ተማሪዎቻችን ከአድልዎ፣ ከጉልበተኝነት፣ ወይም ከወከባ ነፃ የሆኑ ሃይማኖታዊ ወይም ሃይማኖታዊ ያልሆኑ እምነቶቻቸውን እና ድርጊቶቻቸውን የመግለጽ መብት እንዳላቸው በማረጋገጥ ነው።

አገራችን እና የሜሪላንድ ስቴት ስለሃይማኖት ነፃነት መከበር እና በቤተክርስቲያን እና በመንግስት መካከል በሁለቱም ያለውን ልዩነት ለማስጠበቅ ጥልቅና ዘላቂ የሆነ ግዴታ አለባቸው። የመጀመሪያው የዩ.ኤስ. የህገ መንግስት ማሻሻያ አንቀጽ እንደሚለው፡- "ኮንግሬስ የሀይማኖት ምሥረታን የሚመለከት ወይም የሃይማኖትን ነጻነት የሚገድብ/የሚከለክል..." ምንም አይነት ህግ አያወጣም። ይህም ማለት መንግስት አንደኛውን ሃይማኖት ከሌላው በላይ ማራመድ፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት-የለሽ ለይቶ መምረጥ፣ ወይም ሃይማኖትን መቃወም፣ ወይም በሃይማኖት ላይ ጥላቻ መግለፅ  አይችልም።

ት/ቤቶች ለሃይማኖት ገለልተኝነት እንዲኖራቸው አስፈላጊ መሆኑን የዩ.ኤስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አጽንኦት ሰጥቷል። ትምህርት ቤቶች በህዝብ ፊት ለሃይማኖታዊ እውቅና ድጋፍ ባይሰጡም የሁሉንም ተማሪዎች የሃይማኖት ነፃነት መብቶች ማክበርና መጠበቅ አለባቸው። ት/ቤቶች ሃይማኖትን ማራመድ ወይም ማደናቀፍ የለባቸውም፥ ተማሪዎችም እንደዚሁ ኮርሶች ወይም በት/ቤት ስፖንሰር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ዙርያ የምረቃ ሥነ-ሥርዓት ወይም ስብሰባ በሚካሄድበት ስፍራ ከሃይማኖታዊ ማቀንቀን ነፃ የሆነ አካዴሚያዊ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ተማሪዎች ሃይማኖታዊ ወይም ሃይማኖታዊ ያልሆኑ እምነቶቻቸውን እና ተግባሮቻቸውን ከአድልዎ፣ከማስፈራራት ወይም ከትንኮሳ ነጻ ሆነው የማክበር መብት ያላቸው ሲሆን፣MCPS እነዚህን እምነቶች እና ልማዶችን በተገቢ ሁኔታ ለማስተናገድ ቁርጠኛ ነው።

እነዚህ መመርያዎች የተተለሙት፣ በነዚህ ርእሶች ዲስትሪክቱን የሚመሩትን በርካታ የሞንትጎመሪ ካውንቲ  የትምህርት ቦርድ መመርያዎች እና የ MCPS ደንቦች፣ እንዲሁም የስቴት እና የፌደራል ህጎችን በሚመለከት ፈጣን ማጣቀሻ ለመስጠት ነው። ይህ መመሪያ ተማሪዎች በትምህርት ቤት እና ት/ቤት ስፖንሰር በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ላይ እያሉ ስለ ሃይማኖት ዘወትር የሚነሱ ጥያቄዎችን በሚመለከት ከሠራተኞቻችን፣ ከተማሪዎቻችን፣ ከቤተሰቦቻችን፣ እና ከእኛ ማህበረሰብ የሚጠበቀውን ግልጽ እንዲሆን መረጃዎችን በሙሉ በአንድ ላይ ለማጠቃለል ታቅዶ የተዘጋጀ ነው። እነዚህ መመሪያዎች በተለያዩ ህትመቶች መካከል ሊለወጡ እንደሚችሉ እና ወደፊት የሚወጡ ማናቸውም ለውጦች በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማጣቀሻዎች ይተካሉ።

MCPS እነዚህን መመሪያዎች ያዘጋጀው ከሞንጎመሪ ካውንቲ ሥራ አስፈፃሚ የእምነት ማህበረሰብ የሥራ ቡድን እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ነው። ይህ አጋርነት እና ትብብር የተለያዩ የተማሪ ማህበረሰባችንን ሃይማኖታዊ እምነቶች መከባበር ያለንን አድናቆት ማዳበር ይፈልጋል። ሁሉም ቤተሰቦች አክብሮት የሚሰማቸው እና ለመማር፣ ለግንኙነቶች፣ ለአክብሮት፣ እና ለከፍተኛ ልቀት እሴቶቻችን ያለንን ቁርጠኝነት የሚያጎሉበትን ባህል ያዳብራሉ። ብዝሃነት ከእኛ ከፍተኛ ጥንካሬዎቻችን አንዱ መሆኑን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የምናምን ከመሆኑም በላይ በትምህርት ቤቶች አብረን እየተማርን የማህበረሰባችን አስተሳሰብም በዚህ አመለካከት መዳበር እንዳለበት እናምናለን።

እነዚህ መመሪያዎች አጋዥ እንደሚሆኑዎት ተስፋ እናደርጋለን። በዚህ የመመሪያ መጽሐፍ ውስጥ ስለማንኛውም ነገር ጥያቄዎች ካሉዎት እባክዎን በመጀመሪያ ከት/ቤት አስተዳዳሪዎችዎ ጋር ይነጋገሩ። ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት 240-740-3215 ወይም SWC@mcpsmd.org

MCPS ጽ/ቤት የዲስትሪክት አቀፍ አገልግሎት እና ድጋፍ፣ የተማሪ ደህንነት እና ስነ ሥርዓት ማስከበር ዋና ኃላፊን ያነጋግሩ። ለጥያቄዎችዎን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ሊመልሱ ካልቻሉ፣የትምህርት ቦርድ የሥራ ሃላፊን ወይም የቦርድ እንባ ጠባቂን በስልክ ቁጥር 240-740-3030 ወይም boe@mcpsmd.org ማግኘት ይችላሉ።

## ■ ዘወትር የሚቀርቡ ጥያቄዎች

### የሀይማኖት በዓላት ለማክበር ተማሪዎች ሲቀሩ ይቅርታ ይደረግላቸዋል ወይ?

አዎ ቤተሰቦች ቀሪዎችን ለማስታወቅና ለመሰነድ ሁሉንም መደበኛ ሂደቶች መከተል አለባቸው። ለተጨማሪ መረጃ ለኃይ ማኖት በዓላት መቅረት የሚለውን የነዚህን መመርያዎች ክፍል (ገፅ 2) እባክዎ ይመልከቱ።

### ተማሪዎች በበአላት መቅረቶች ምክንያት ለጎደለ ስራ መተካት ይችላሉ ወይ?

አዎ ቤተሰቦች ለጎደለ ስራ ማካካሻ ለማሳካት ከልጃቸው ት/ቤት ጋር አብረው መስራት አለባቸው። እባክዎ ይበልጥ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ስለ ሃይማኖት በዓላት መቅረት የሚለውን የዚህን መመርያ ክፍል (ገፅ 2) ይመልከቱ።

### ተማሪዎች በትምህርት ቀን ፀሎት ማድረግ ይችላሉ ወይ?

እዎን፣ በተወሰኑ ሁኔታዎች። እባክዎ ለልዩ ተጨማሪ መረጃ ፀሎትና ሃይማኖታዊ አለባበስ የሚለውን የዚህን መመርያ ክፍል (ገፅ 3) ይመልከቱ።

### ተማሪዎች ከሃይማኖታቸው ጋር የተዛመደ ልብስ መልበስ ይችላሉ ወይ?

አዎ የቦርድ ፖሊሲዎች፣ MCPS መመሪያዎችና ደንቦች ድንጋጌ መሠረት ተማሪዎች ስካርፍ፣ ሂጃብ፣ ያርሙሌክስ፣ ፓትካስ፣ ኩፊስ ወይም ከሃይማኖቶቻቸው ጋር የሚዛመዱ ሌሎች አልባ ሳትን መጠቀም ይችላሉ። ለልዩ ተጨማሪ መረጃ ፀሎትና የሃይ ማኖት አለባበስ የሚለውን የነዚህን መመርያዎች ክፍል (ገፅ 3) እባክዎ ይመልከቱ።

### በት/ቤት ስራዎች የሀይማኖት ርእሶች መወያያ ሊሆኑ ይችላሉ ወይ?

አዎ መግለጫዎቻቸው የተመደበላቸውን የት/ቤት ሥራ መስፈርቶችን እስካሟሉና ለርዕሱ ተዛማጅ እስከሆኑ ድረስ በዚህ የመመሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተብራሩትን ሌሎች መመሪያዎች እስከተከተሉ ድረስ ተማሪዎች በትምህርት ቤት እንዲሠሩ የተሰጣቸው የትምህርት ሥራ ውስጥ ሃይማኖታዊ እምነታቸውን መግለጽ ወይም ሃይማኖተኛ አለመሆናቸውን ሊገልጹ ይችላሉ። በተጨማሪ፣ በስነፅሁፍ፣ ታሪክ፣ እና በኪነጥበባት ውስጥ ስለ ሀይማኖት ያልተዛቡና ሀቀኛ ትምህርቶች የስርአተትምህርት አካል ሊሆኑ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ ሃይማኖት በትምህርት ፕሮግራም ውስጥ የሚለውን የነዚህን መመርያዎች ክፍል (ገፅ 3) እባክዎ ይመልከቱ።

### ት/ቤቶች የተማሪዎችን ሀይማኖት-ነክ የአመጋገብ ማእቀቦችን ያስተናግዳሉ ወይ?

አዎ ት/ቤቶች ከሀይማኖት ጋር የተያያዙ የአመጋገብ ገደብ ካለቸው ተማሪዎች ጋር ያለማቋረጥ ይሰራሉ። ለተጨማሪ መረጃ ምግብና የሃይማኖት ስነ ስርአትየሚለውን የነዚህን መመርያዎች ክፍል (ገፅ 5) እባካችሁ ተመልከቱ።

### ተማሪዎች የሀይማኖት የመረጃ ቁሳቁሶችን ማሰራጨት ይችላሉ ወይ?

አዎ ተማሪዎች የሃይማኖት የመረጃ ቁሳቁሶችን ልክ እንደ ሌሎች ከት/ቤት እንቅስቃሴዎች ጋር ያልተያያዙ የመረጃ ቁሳቁሶች ደንቦች መሰረት ማሰራጨት ይችላሉ ። ተማሪዎች ቁሳቁሶችን የት፣ መቼ፣ እና እንዴት እንደሚሰራጩ የት/ቤት ህጎችን ማክበር ኣለባቸው። ለተጨማሪ መረጃ የሃይማኖት መረጃ ቁሳቁሶች ስርጭትየሚለውን የነዚህን መመርያዎች ክፍል (ገፅ 5) እባካችሁ ተመልከቱ።

### በት/ቤት ከትምህርት ውጭ ሀይማኖታዊ ክበቦች ይፈቀዳሉ ወይ?

አዎ አንደ ሌሎች በት/ቤት ከሚቀርበው አርእስት ጋር ቀጥታ ግንኙነት የሌላቸው የተማሪ ከትምህርት-ጊዜ-ውጭ ቡድኖች፣ ተማሪዎች ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ ክበቦች የማደራጀት ወይም ተሰብስቦ የሃይማኖት ስብሰባዎች፣ የፀሎት ቡድኖች፣ ወይም ሌሎች ሃይማኖታዊ ልምዶችን ከትምህርት-ጊዜ-ውጭ የማክበር መብት አላቸው። እነዚህ ሃይማኖት-ነክ ከትምህርት-ጊዜ-ውጭ ስብሰባዎች ወይም ክበቦች በተማሪዎች የሚመሩ መሆን ኣለባቸው። ለተጨማሪ መረጃ እና ልዩ መመርያ፣ ከስርእተት ምህርት ውጭ የተማሪ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች የሚለውን የነዚህን መመርያዎች ክፍል (ገፅ 6) እባካችሁ ተመልከቱ።

## ■ በሃይማኖት በኣላት ምክንያት መቅረት

### ክትትል እና የሃይማኖት በዓላትን ለማክበር መቅረት

በየእለቱ በት/ቤት ተገኝቶ ክትትል ማድረግ ለተማሪ ስኬት ወሳኝ ነው። ቢሆንም፣ ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች፣ የሃይማኖት በዓላትን ለማክበር ጨምሮ፣ ኣልፎ ኣልፎ ከት/ቤት እንደሚቀሩ MCPS ይገነዘባል። አነዚህ የተፈቀዱ መቅረቶች ናቸው፣ ተማሪዎችም ለጎደሉ ስራዎች መተኪያ አንዲያደርጉ ይፈቀድላቸዋል። ተማሪዎች ከት/ቤት ከቀሩ፣ ትቤት ከተመለሱበት በሶስት ቀኖች ውስጥ የፅሁፍ ማብራርያ የሚሰጥ ማስታወሻ ከወላጅ/ኣሳዳጊ ማምጣት አለባቸው።

ሃይማኖታዊ በዓል ከማክበር ጋር በተያያዘ ምክንያት ዘግይቶ መምጣት ወይም አስቀድሞ ለመለቀቅ ተቀባይነት ያላቸውን ጥያቄዎች MCPS ያስተናግዳል፣ ነገር ግን በወላጅ/አሳዳጊ መፈቀድ አለባቸው።

ምንም እንኳን ማንኛውም የኣትሌቲክ ክውነት ወይም ልምምድ ተሳትፎ በኣብዛኛው በክውነቱ ወይም በልምምዱ እለት ኣትሊቶቹ የተመደበላቸውን የትምህርት ፕሮግራም እንዲከታተሉ ተፈላጊ ቢያደርገውም፣ እንደ የሃይማኖት በኣል ኣከባበር የመሰሉ ኣስቀድመው የተመደቡ እንቅስቃሴዎች ያሏቸው ተማሪዎች፣ ከት/ቤታቸው በተቀዳሚ ፈቃድ እስካገኙ ድረስ፣ በኣትሌቲክ ክውነቶች ወይም ልምምዶች በቀሪው ቀን እንዲሳተፉ ይፈቀድላቸዋል።

ነፃ የሃይማኖት ኣምልኮ ህገ መንግስታዊ መብት ስለሆነ፣ በትክክል የትምህርት ክትትል ሽልማት ለሚገባቸው MCPS ት/ቤቶች መቅረት ለተፈቀደላቸው የሃይማኖት በዓላት ቀሪ ለሆኑ ተማሪዎች ሽለማቶቹን ላይከለክሉ ይችላሉ።

ማጣቀሻዎች፡-
MCPS ደንብ JEA-RA፣ የተማሪ ትምህርት ክትትል.

### በሃይማኖት በዓላት ማክበር ምክንያት ከቀሩ በኋላ የመተኪያ ስራ

ተማሪዎች ከት/ቤት በመቅረታቸው ላልሰሩት ስራ ሃላፊነት ኣለባቸው ባጠቃላይም እንዲተኩ ይጠበቅባቸዋል። የሃይማኖት በዓላት ሲያከብሩ የሚያመልጣቸውን ለመተካት መራዘሚያዎች ወይም ሌላ መገልገያዎች ለማሳካት አስቀድመው ፕላን ማድረግ ለተማሪዎችና ለወላጆች/አሳዳጊዎች የተሻለው ኣማራጭ ነው። ቢሆንም፣ MCPS ይህ ሁልጊዜ ተግባራዊ ነው ወይም ሊሆን ይችላል ማለት እንዳልሆነ ይገነዘባል። ቀሪነቱ ፈቃድ ካለው፣ የተማሪው/ዋ መምህር ያመለጠውን ጊዜ ለመተካት ተማሪው(ዋ)ን ያግዘዋል/ታግዘዋለች/ያግዛታል/ታግዛታለች፣ ዳግመ-ፈተና ያቀርባል/ታቀርባለች፣ ወይም በተማሪው/ዋ የሃይማኖት በኣል ሲከበር መፈፀም ለነበረበት የክፍል ስራ ወይም የቤት ስራ ማራዘሚያ ጊዜ መስጠት። እያንዳንዱ ሁኔታ አንድ ባንድ መታየት እንዳለበት የተጠበቀ ሆኖ፣ ከተፈቀደ የሀይማኖት በአል ለማክበር መቅረት በኋላ ተማሪዎች እስከ ሶስት የትምህርት ቀኖች ለመተኪያ የማራዘም ብቃት ይኖራቸዋል።

በተጨማሪ፣ የቤት ስራ ሲሰጡ፣ ት/ቤቶች ለማህበረሰባችን አባላት ኣስፈላጊ የሆኑትን ባህላዊ፣ የዘር፣ የሃይማኖት፣ እና ሌሎች በዓላት ወይም ክውነቶች ግንዛቤ ውስጥ እንዲያስገቧቸው ያስፈልጋል። ሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎችን ሃይማኖታዊ፣ ብሄረሰባዊ እና ባህላዊ ቅርስ ጋር የተያያዙ አንዳንድ በዓላትን ጨምሮ የመታሰቢያ ቀናትን ዝርዝር አዘጋጅቷል፣ በዚህ ድረገጽ ላይ ይገኛልwww.montgomerycountymd.gov/mcg/commemorations.html ።

ፍትኃዊነትንና-ሚዛናዊነትን የሚያበረታታው ክፍል-The Equity Initiatives Unit ለሠራተኞች እና ለሌሎች MCPS ማህበረሰብ አባላት ሊጠቅማቸው የሚችል ስለ በርካታ የመታሰቢያ/የክብረበዓላት ቀኖችን የኋላ-የመነሻ ታሪክ መረጃ የሚገልጽ ዶኩመንት አለው። MCPS ድረገጽ ላይ የሚገኘው የቀን መቁጠርያ Days of Commemoration/የክብረ በዓላት ቀኖችን MCPS የት/ቤት መዘጋት በመረጃነት በተጨማሪ፣ ለሰራተኞች፣ ለተማሪዎች፣ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች እና የማህበረሰብ አባላት ማጣቀሻ እንዲሆኑ ያደርጋል። የቀን መቁጠርያው በዚህ ድረገጽ ላይ ይገኛል፡-www.montgomeryschoolsmd.org/info/calendars/

## ■ ፀሎት እና ሃይማኖታዊ አለባበስ

### ፀሎት በት/ቤት

እነዚህ ተግባራት በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ፥ እና በተማሪ ፍላጎት የሚከናወኑ፥ የክፍል ትምህርትን ካላደናቀፉ፥ ሌሎች የት/ቤት እንቅስቃሴዎችን ወይም የሌሎችን መብት በቁሳዊ ሁኔታ እስካላሰናከሉ ወይም እስካልገቡ ድረስ ተማሪዎች ለመጸለይ እና ሃይማኖታዊ አመለካከቶቻቸውን ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ለመወያየት ነፃ ናቸው። ለምሳሌ፦ እንድ ተማሪ ከምግብ በፊት ወይም ከፈተና በፊት መደበኛ ባልሆኑ ቦታዎች፣ እንደ ካፌቴርያዎች ወይም መተላለፍያዎች፣ ተማሪዎች ሃይማኖታዊ ባልሆኑ እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ በተፈቀደላቸው መጠን፣ መፀለይ ወይም የሃይማኖት ፅሁፎችን ማንበብ ይችላል/ትችላለች፤ ወይም አንድ የተማሪ አትሌት ከውድድር በፊት ወይም ተችዳወን ወይም የጎል ግብ ካገኘ(ች) በኋላ ውድድሩን ከመጠን በላይ እስካላዘገየው ወይም እስካልረበሸ ወይም በሌሎች አትሌቶች ወይም ተመልካቾች መብቶች ጣልቃ እስካልገባ ድረስ መፀለይ ይችላል/ትችላለች። ምንም እንኳን ተማሪዎች የመፀለይ መብታቸውን በትምህርት ቀን ወይም ከት/ቤት በተያያዙ እንቅስቅሴዎች ማስከበር ቢችሉም፣ ሌሎችን በፀሎት፣ ስብከት፣ ወይም በሌላ የሀይማኖት እንቅስቃሴ እንዲሳተፉ ወይም እንዲያዳምጡ ማስገደድ፣ ማዋከብ፣ ወይም መገፋፋት አይችሉም። ለምሳሌ፦ በተማሪ-የተመሩ ፀሎቶች በት/ቤቱ የህዝብ ማስታወቂያ ስርአት ለሁሉም ክፍሎች ማሰራጨት አይፈቀድም።

አንድ ተማሪ ለፀሎት የሚሆን ፀጥተኛ ቦታ ከጠየቀ/ች፣ ቦታ እስካለ ድረስ፣ የተማሪ ደህንነት ለማረጋገጥ የሚቆጣጠር አግባብ ያለው ሰራተኛ እስካለ ድረስ፣ እና የትምህርት ሂደት እስካልረበሸ ድረስ፣ ት/ቤቶች ጥያቄውን ለማስተናገድ ተገቢ ጥረት ያደርጋሉ። ይህም በሚድያ ማእከል፣ ባዶ የመማርያ ክፍል፣ ወይም በሌላ ክፍል ውስጥ አንድ የፀጥታ የተሞላበት ስፍራ ማለት ሊሆን ይችላል።

ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች መገንዘብ የሚኖርባቸው MCPS መምህራን፣ አስተዳዳሪዎች፣ እና ሌሎች ሰራተኞች የተማሪ ፀሎቶች ወይም ሌሎች የተማሪ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች በትምህርት ሰአቶች ወይም በት/ቤት ስፖንሶርድ በሆኑ ክውነቶች አያደራጁም፣ አይመሩም፣ አያነሳሱም፣ አይደገፉም፣ ወይም በተግባር አይሳተፉም። በተማሪ ፀሎቶች ወይም ሌሎች በተማሪ የሚመሩ የሃይማኖት እንቅስቃሴዎች MCPS ሰራተኞች ሊገኙ ይችላሉ አላማዎቹ ግን የተማሪንና የት/ቤት ደህንነት ለማረጋገጥ ለመከታተልና ቁጥጥር ለማድረግ ብቻ ነው።

### ሃይማኖታዊ አለባበስ

ተማሪዎች ትምህርት ቤት ሲመጡ በማህበረሰብ የአለባበስ እና የማጌጥ መስፈርቶች እና በትምህርት አካባቢ እና በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍን በማይረብሽ ወይም በማይከለክል መልኩ በአግባብ የመልበስ እና የመዋብ ሀላፊነት አለባቸው። ተማሪዎች የአለባበስ ዘይቤያቸው ከሚከተለው መመሪያ ጋር ካልተጣረሰ ከሃይማኖታቸው ጋር የሚገናኝ ወይም ሃይማኖታዊ መልዕክቶችን የያዙ ሸማ፣ ሂጃብ፣ ያርሙልክስ፣ ፓትካ ወይም ሌላ ልብስ ወይም ጌጣጌጥ እንዲለብሱ ይፈቀድላቸዋል። የተማሪዎች አለባበስ መሆን የሌለበት —

- የራስን ወይም የሌሎችን ጤና እና/ወይም ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥል ወይም ሊያሰጋ የሚችል፤
- የጥላቻ ወይም አድሏዊ መልዕክቶችን ማሳየት ወይም አድሏዊ ምልክቶችን ወይም ምስሎችን የሚያመለክት፣
- የአንድን ኮርስ ሒደት ወይም እንቅስቃሴ አግባብነት ያለው መስፈርት ማሟላት የማይችል፣
- ከወሮበሎች/ጋንጎች ቡድን ጋር የተያያዘ፣
- ሴሰኛ፣ ባለጌ፣ ጸያፍ፣ ወይም ገላጭ ወይም ወሲባዊ ተፈጥሮን አጋልጦ የሚያሳይ መሆን የለበትም፣ ወይም
- MCPS ደንብ IGO-RA፣ የአልኮል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ እና ሌሎች የአደንዛዥ እፅ አጠቃቀም መመሪያዎችን በተመለከተ MCPS ንብረት ላይ ለተማሪዎች የተከለከሉ ወሲባዊ ድርጊቶችን ወይም ትምባሆ፣ አልኮል፣ ካናቢስ ወይም ሌሎች መድሃኒቶችን ማስተዋወቅ  የተከለከለ ነው።

በተቻለ መጠን ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን (ወይንም ወላጆቻቸውን/አሳዳጊዎቻቸውን ወክለው) አንዳንድ ልብሶችን ለመልበስ ወይም ላለመልበስ ፈቃድ ከጠየቁ ከሃይማኖታዊ እምነታቸው ጋር የማይጣጣሙ ናቸው ብለው የሚያስቡትን የአካል ማጎልመሻ ትምህርት ወይም ትምህርት ቤት ስፖንሰር በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ላይ በተገቢ ሁኔታ ማስተናገድ አለባቸው። የዚህ አይነቶቹ መስተንግዶዎች/ማመቻቸቶች የተማሪን በአንድ እንቅስቃሴ መሳተፍ አይከለክሉም/አያግዱም። ለምሳሌ፦ የሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ አትሌቲክስ ማህበር በት/ቤቶች መካከል በሚካሄዱ ውድድሮች የሚሳተፉ አትሌቶችን "የራስ መሸፈኛ፣ ጥምጣም፣ ወይም ሌላ አስፈላጊ የሆኑ ሀይማኖታዊ ልብስ ለተጫዋቾች ወይም ለሌሎች ሻካራ፣ ጠንካራ፣ ወይም አደገኛ ያልሆነ፣ እናም በጨዋታ ጊዜ ተመንጥቆ የማይሄድ/ተገፎ የማይወድቅ አይነት አለባበስ እንዲለብሱ" ይፈቅዳል። የአትሌቲኮች መስተንግዶዎችን የሚመለከቱ ስለሌሎች ጥያቄዎች፣ እባካችሁ የት/ቤት አትሌቲክ ዳይሬክተር ወይም MCPS አትሌቲክ ክፍልን ያማክሩ።

## ■ ሃይማኖት በትምህርት አሰጣጥ ፕሮግራም ውስጥ

### ሃይማኖት በት/ቤት ስራዎች ውስጥ

መግለጫዎቻቸው ለአርእስቱ አስፈላጊ እስከሆኑና የስራውን ግዴታዎች እስካሟሉ ድረስ ተማሪዎች የሃይማኖት እምነቶቻቸውን ወይም አለማመናቸውን በት/ቤት ስራዎች ለመግለፅ ነፃ ናቸው። በት/ቤት ስራዎች ግምገማ ላይ፣ መምህራን በተማሪዎች ስራ ውጤቶች ላይ ከሃይማኖት ይዘት በመነሳት አድልዎ አይፈፅሙም። የት/ቤት ስራ የሚመዘነው በመደበኛ አካዴሚያዊ መመዘኛዎችና በሌሎች ህጋዊ የትምህርት ጥቅሞች ነው። ለምሳሌ፦ አንድ ስራ ግጥም መፃፍን የሚያካትት ከሆነ፣ ተማሪ ያቀረበ/ችው በፀሎት መልክ የተፃፈ ግጥም ስራ (እንደ መዝሙረ ዳዊት ወይም ፒዩት/piyyut) በአካዴሚያዊ መመዘኛዎች (እንደ የስነፅሁፍ ልቀት) ይገመገማል እንጂ በግጥሙ የሃይማኖት ይዘት በመነሳት አይ(ት)ቀጣም ወይም አይ(ት)ሸለምም።

### በሃይማኖት ምክንያቶች ከትምህርት ፕሮግራም የመቅረት ፈቃድ ጥያቄዎች

ተማሪዎች ከቤተሰብ ሃይማኖታዊ እና/ወይም ሌሎች ልማዶች ጋር የሚጋጩ ቁሳቁሶችን ወይም ተግባራትን ከሚያካትቱ በትምህርት ክፍል የሚከናወኑ ፓርቲዎች ወይም የነፃ ጊዜ ዝግጅቶች ከመሳሰሉ ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ነጻ ሊደረጉ ይችላሉ።

ነገር ግን፣ MCPS በሃይማኖታዊ እና/ወይም በሌሎች ተቃውሞዎች ምክንያት የሚፈለገውን ሥርዓተ ትምህርት ከመማር ወይም ሥርዓተ-ትምህርታዊ ቁሳቁሶችን ከመጠቀም ነፃ የመሆን ጥያቄዎችን ማስተናገድ አይችልም።

## በት/ቤት ስለ ሃይማኖት ወይም የሃይማኖት በዓላት ማስተማር

ት/ቤቶች ልጆች ከራሳቸው የተለዩ ባህሎችንና ቅርሶችን እንዲማሩና እንዲያደንቁ የሚችሉበት አካባቢ ማዳበር እንዳለባቸው MCPS ያምናል። በዚህ አላማም፣ MCPS ስርአተትምህርት በስነፅሁፍ፣ በታሪክ፣ በሰብአዊ ጥናቶች፣ እና በኪነጥበባት የሃማኖቶችን ሚና እውቅና ይሰጣል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስርአተ ትምህርት ስለ መንግስት እና የሃይማኖት ነፃነት መካከል ስላለው ግንኙነት የተማሪዎችን ግንዛቤ ያዳብራል። በተገኘ ቁጥር፣ የሃይማኖት ገፅታዎች ውይይት የሚደረግባቸው ስለ የሃማኖቶች ታሪክና አመዛዛኝ/comparative ጥናት የሚመረጡ/elective የክፍል ትምህርቶች ተማሪዎች መከታተል ይችላሉ።

ተማሪዎች ስለሃይማኖት ሲማሩ፣ መጠበቅ ያለባቸው የትምህርት እንቅስቃሴዎች ርተአዊ፣ ያልተዛቡ፣ እና ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ሆነ ኢሀይማኖታዊ እምነቶች የማያንቋሽሹ ናቸው። የህብረ-ብዙ ህብረተሰብ አይነተኛ ባህርይ የተማሪዎችን የተለያዩ እምነቶች ማክበር ነው። በመምህራን፣ ተማሪዎች፣ እና በእንግዳ ተናጋሪዎች የሚሰጡ ንግግሮች የተለዩ ሃይማኖታዊ መልእክቶችን ከሌሎች ሃይማኖትዊ ወይም ከሃይማኖታዊ ስርዓት ይሻላሉ ብሎ መስበክ ወይም ማቀንቀን የለባቸውም። ተማሪዎች ስለ ሃይማኖት ባህሎች አስተያየታቸውን ለማካፈል መምረጥ ወይም ላለመምረጥ ይችላሉ። ተማሪዎችም በበኩላቸው ለሃይማኖታዊ ልምዶች ቃል አቀባዮች ወይም ወካዮች እንዲሆኑ አንጠየቅም ብለው መጠበቅ አለባቸው። ለእንደዚህ አይነቱ ሁኔታ ተማሪዎችን ለይቶ ማውጣት ምቾት እንዳይሰማቸው ሊያደርግ ይችላል፣ እናም የአንድን ተማሪ የሃይማኖት ተሞክሮ የጠቅላላ ቡድን ተደርጎ መወሰድ የለበትም።

እንደ የማስተማርያ መሳርያ ወይም መገልገያ፣ ት/ቤቶች የሃይማኖት ምስሎች/symbols እንደ የሃይማኖት ወይም ባህላዊ ናሙናዎች አድረገው ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ነገር ግን እነዚህ የትምህርት መሳርያዎች ወይም መገልገያዎች መታየት ያለባቸው አግባብ ያለው የመማርያ ክፍል ትምህርት ለማጀብ ለጊዜያዊ ወቅት ብቻ መሆን አለበት።

የትምህርት አካል በማድረግ፣ ት/ቤቶች ስለሃይማኖታዊ በአላት እንደ እለታዊ ሃቅ/factual manner ማስተማር ይችላሉ። የት/ቤት እንቅስቃሴዎች የበአልን አለማዊ/መንፈሳዊ ያልሆኑ ገፅታዎችን ማንፀባረቅ ይችላሉ፣ ነገር ግን የሃይማኖት እንቅስቃሴዎች በሃይማኖታዊ ልምድ ወይም ክውነት መሳተፍን ላያካትት ይችላል። የተለያዩ ሃይማኖት ተከታይ ተማሪዎች፣ ወይም ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው፣ ተማሪዎች ከተወሰኑ የሃይማኖት እንቅስቃሴዎች ከመሳተፍ ይቅርታ እንዲደረግላቸው መጠየቅ ይችላሉ። መምህራን ጥያቄ ላቀረቡ ተማሪዎች አማራጭ እንቅስቃሴ በማዘጋጀት እነዚህን ጥያቄዎች ለማክበር መስራት አለባቸው። የልደት ቀኖች ወይም ብዙዎች አለማዊ ናቸው ብለው የሚገነዘቧቸው ሌሎች ወቅቶች፣ እንደ ሃሎዊን እና ቫሌንቲንስ ዴይ፣ በሌሎች እይታ የሃይማኖት አዝማሚያነታቸዉ ያመዝናል ተብለው ሊታዩ ይችላሉ። ት/ቤቶች በነዚህ አካባቢ እንቅስቃሴዎች ሊኖራቸው ይፈቀድላቸዋል—አለማዊ ጠባይ እስከያዙ ድረስ—መሳተፍ ለማይፈልጉ ተማሪዎችም ይቅርታ ሊያደርጉላቸው ይችላሉ።

## ሃይማኖት በት/ቤት ስብሰባዎች እና በሙዚቃ በአላት

ልዩ የት/ቤት ክውነቶች፣ ስብሰባዎች፣ የሙዚቃ በአሎች፣ እና ፕሮግራሞች አለማዊና ያልተዛባ የትምህርት ፕሮግራም ለማራመድ መተለም አለባቸው እናም በአንድ ሃይማኖት ወይም የሃይማኖት በአል ማተኮር የለባቸውም። ለምሳሌ፣ የፕሮግራሙ አጠቃላይ መልእክት/effect ከሀይማኖታዊ ስርአት ውጪ እስከሆነ ድረስ የሃይማኖት ሙዚቃ በዊንተር የሙዚቃ በአል መቅረብ ይችላል፣ እናም ኢሃይማኖታዊ ሙዚቃ ሚዛናዊና ሁሉን የሚያካትት አካሄድ አካል ሆኖ በተጨማሪ ይካተታል።

ትላልቅ ስብሰባዎች ወይም ፕሮግራሞች የተማሪዎች የሙዚቃ ትርኢቶች (ባንዶችን) ወይም ሌሎች የሙዚቃ ቡድኖችን በሚያካትቱበት ጊዜ፣ በጉባኤው ወይም በፕሮግራሙ ላይ የሚጫወቱ ተማሪዎች ሃይማኖታዊ ሙዚቃ ለእምነታቸው አግባብ እንዳልሆነ ከተሰማቸው በአግባቡ እንዲታይላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ። የመስተንግዶ ጥያቄዎችን ሲያስተናግዱ፣ የት/ቤት ሰራተኞች ተማሪዎችን ከሚያሳፍር ሁኔታ፣ ወይም ከመጋጨት ለማዳን ከተማሪዎችና ከወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው ጋር መመካከር አለባቸው።

በስብሰባዎች የተማሪ ወይም የእንግዳ ተናጋሪዎች መመረጥ ያለባቸው ሃይማኖትን በማይደግፉ ወይም በማይቃወሙ በርትአዊ መስፈርቶች ተመስርቶ መሆን አለበት። የተማሪን ወይም የእንግዳ ተናጋሪን አስተያየቶች (ሃይማኖታዊ ይሁኑ አይሁኑ) ት/ቤቱ ይደግፋል በማለት ወደ ሌሎች ተማሪዎች፣ ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው፣ ወይም እንግዶች የሚተላለፈውን አስተያየት ለማስወገድ ት/ቤቶች ተገቢ፣ ነፃ የሆኑ ማስተባበያዎች ማድረግ አለባቸው። በተጨማሪ፣ ሃይማኖት-ነክ ርእሶች ወይም በአላት የሚያካትቱ ስብሰባዎችና ሌሎች የት/ቤት ክውነቶች በት/ቤቶች ፕሮግራም እድሜ ታሳቢ እንደሚሆን ወላጆች/አሳዳጊዎች መገንዘብ አለባቸው። ምንም እንኳን የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች በርትአዊ መንገድ እንዲናገሩ የተመረጡ ተማሪዎች ወይም እንግዶች አስተያየቶችን ት/ቤት የማይደግፍ መሆኑን ሊገነዘቡ ቢችሉም፣ የመካከለኛና የኤሌሜንተሪ ተማሪዎች፣ የት/ቤት ሰራተኞች በአግባቡ ማስተባበያ ቢሰጡም፣ ይህን ለመለየት መቻላቸው አጠራጣሪ ነው።

# ■ ምግብና የሃይማኖት በአል

## ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ የምግብ አይነት ገደቦችና ፆም

ተማሪዎች፣ ወይም ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው፣ አይማኖት-ነክ የአመጋገብ ገደብና ፆምን ይሚያካትቱ ተቀባይነት ያላቸውና ተግባራዊ ሊደረጉ የሚችሉ መስተንግዶዎች እንዲያደርጉ ት/ቤቶችን መጠየቅ ይችላሉ። MCPS የምግብና የአመጋገብ አገልግሎቶች ክፍል የአመጋገብ ገደቦች ያሏቸው ተማሪዎች በምግቦች ተለጣፊ ማስታወቂያ በማድረግ/labeling food እና/ወይም ለቁርስ፣ ለምሳ፣ እና ለቅምሻዎች/snacks እንደ የአሳማ ስጋ-ነፃ፣ የተለያዩ አማራጮች በማቅረብ ማገዝ ይችላሉ፣ ነገር ግን ት/ቤቶች የአንድን ተማሪ ልዩ ሃይማኖታዊ ፍላጎቶችን ለማርካት ልዩ ምግቦች እንዲያዘጋጁ አይጠበቅባቸውም። የበለጠ መረጃ ለማግኘት ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፦www.montgomeryschoolsmd.org/departments/food-and-nutrition/.

በተመሳሳይ፣ በሃይማኖት ምክንያት የሚፆሙ ተማሪዎች፣ ተገቢ የሰራተኛ ቁጥጥር እስካለ ድረስ፣ በምሳ ሰአት ከካፌቴርያ ይልቅ ወደ ሚድያ ማእከል ወይም ወደ ሌላ የተለየ ቦታ እንዲሄዱ ሊፈቀድላቸው ይችላል። በተጨማሪ፣ በሃይማኖት ምክንያት የሚፆሙና በአካል ማሰልጠኛ ትምህርት ከከባድ እንስቃሴዎች ክመሳተፍ ይቅርታ እንዲደረግላቸው የሚጠይቁ ተማሪዎች መጠነኛ መስተንግዶ እንዲደረግላቸው ይገባል። ተማሪዎች የተጠየቀውን ከፆም ጋር የተያያዘ መስተንግዶ የሚለይ የፅሁፍ ማብራርያ የሚያቀርብ ማስታወሻ ከወላጅ/አሳዳጊ ወደ ት/ቤት ማምጣት አለባቸው።

## ■ የሀይማኖታዊ መረጃያዊ ቁሳቁሶች ስርጭት

### ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ የመረጃ ቁሳቁሶች ለማሰራጨት የተማሪ ጥያቄዎች

ተማሪዎች ከት/ቤት ስርአተትምህርት ወይም እንቅስቃሴዎች ጋራ ያልተያያዘ ሌላ መረጃያዊ ቁሳቁስ ለማሰራጭት በተፈቀደላቸው ተመሳሳይ ሁኔታዎች መሰረት ሃይማኖት-ነክ መረጃያዊ ቁሳቁሶች ለት/ቤት ጓዶቻቸው ሊያሰራጩ ይችላሉ። ይህም ማለት ስርጭቱ በስንት ሰዓት ሊከናወን እንደሚችል፣ የት ቦታ እንደሚቻል፣ እና እንዴት ሊደረግ እንደሚችል ት/ቤቶች መደንገግ ይችላሉ፣ እነዚህ ጊዜ፣ ቦታ፣ እና የስነምግባር ገደቦች በሁሉም ከት/ቤት-ጋር-ባልተያያዙ የተማሪ መረጃያዊ ቁሳቁሶች ተግባራዊ እስከሆኑ ድረስ ማለት ነው።

እነዚህ እንደ ፖለቲካ ቁሳቁሶች ወይም ከትምህርት ቤት ጋር ያልተዛመዱ ሌሎች ማናቸውም የመረጃ ቁሳቁሶችን ለማሰራጨት ጊዜን፣ ቦታን እና የሥርጭት ሁኔታዎችን የሚገልጹ ጉዳዮች ከትምህርት ክፍለ ጊዜ ውጭ ብቻ መሆን እንዳለበት በ MCPS ደንቦች እና ህጎች ውስጥ ተንፀባርቋል። ለምሳሌ፡- በመተላለፊያ መንገዶች፣ በካፌቴሪያ፣ የተፈቀዱ ኮሪዶሮች፣ ወይም የተማሪ አመራር ክፍሎች ወይም መስኮች መረጃያዊ ቁሳቁሶች ለማሰራጨት ት/ቤቶች ለተማሪዎች ሊፈቅዱላቸው ይችላሉ። የሆነ ሆኖ፣ ተማሪዎች ከት/ቤት-ጋር ያልተያያዙ መረጃያዊ ቁሳቁሶች በመማርያ ክፍሎች፣ የሚድያ ማእከል፣ ወይም በሌሎች ት/ቤት ክፍሎች በትምህርት ቀን ማሰራጨት የለባቸውም፣ (1) ክፍሉ እንደ የበጎ-ፈቃደኛ መሰብሰብያ ቦታ ተብሎ ጥቅም ላይ እስከዋለ ድረስ ወይም (2) መረጃያዊ ቁሳቁሱ መመርያ ክፍል ውስጥ እንደ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም አካል ወይም የበጎ-ፈቃደኛ መድረክ ወይም በተማሪዎች የተካሄደ ሴሚናር ካልሆነ በስተቀር። በተጨማሪ፣ ተማሪዎች ሀይማኖታዊም ሆነ ፀያፍ፣ ስም-አጥፊ፣ የትምህርት አካባቢ ረባሽ፣ ወይም በት/ቤት አካባቢ የሚገኙ የሌሎችን መብቶች የሚደፍሩ መረጃያዊ ቁሳቁሶችን በት/ቤት መቼት ማሰራጨት አይችሉም።

ማጣቀሻዎች፡-

MCPS ደንብ JFA-RA፥ የተማሪ መብቶችና ሀላፊነቶች

MCPS ደንብ CNA-RA የመረጃ እና የማስታወቂያ ቁሳቁሶችን በሚታይ ቦታ ስለማስቀመጥ-ስለማሳየት።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ-MCPS ደንብ KEA-RA፣ በፖለቲካ ዘመቻዎች መሳተፍ እና የዘመቻ ቁሳቁሶችን ማሠራጨት

## ■ ከስርአተ ትምህርት ውጭ የትርፍ ሠዓት የተማሪ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች

### ከሃይማኖት ጋር የተያያዙ ከስርአተ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችና ክበቦች

ተማሪዎች ሃይማኖት-ነክ ከስርኣተ ትምህርት ውጭ ክበቦች ለማደራጀት ወይም ሃይማኖታዊ ስብሰባዎች፣ የፀሎት ቡድኖች፣ ወይም ሌሎች የሃይማኖት ልምዶች ማክበር ትምህርት ከሚሰጥበት ጊዜ ውጭ የማካሄድ መብት ኣላቸው። እነዚህ ሃይማኖት-ነክ ከስርኣተትምህርት ውጭ ስብሰባዎች ወይም ክበቦች በተማሪዎች የሚመሩ መሆን ኣለባቸው። MCPS ሰራተኞች የተማሪና የት/ቤት ደህንነት ለማረጋገጥ ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርጉ ይችላሉ፣ ነገር ግን ከስርአተትምህርት ውጭ ስብሰባዎች ወይም ክበቦች በሚካሄዱ ፀሎቶች ወይም ሌሎች ሃይማኖታዊ ተግባሮች ማደራጀት፣ መምራት፣ ማነሳሳት፣ መደገፍ፣ ወይም በተግባር መሳተፍ አይገባቸውም።

በተማሪዎች-መሪነት የሚካሄዱ ማናቸውም ኃይማኖታዊ የሆኑ፣ ተጨማሪ ሥርዓተ ትምህርት ክለቦች ወይም እንቅስቃሴዎችን በት/ቤት ክልል ውስጥ በቂ ቦታ ለማግኘት በቅድሚያ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተዳደርን ማነጋገርና ማሳወቅ አለባቸው። ልክ እንደ ሌሎች ከስርኣተ ትምህርት ውጭ በት/ቤት ውስጥ ትምህርት ከሚሰጥበት ርእስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው የተማሪ ቡድኖች፣ የተማሪ ሃይማኖታዊ ቡድኖች ለት/ቤት መገልገያዎች፣ መሳርያ፣ እና አገልግሎቶች እኩል መዳረሻ ኣላቸው። ይህም የማስታወቂያ ሰሌዳዎችን፣ ኮምፒውተሮችን፣ እና የት/ቤት ጋዜጣ ማስታወቂያዎችን ያካትታል፣ እንደዚህ አይነቱ መዳረሻ በት/ቤት ውስጥ ትምህርት ከሚሰጥበት ርእስ ጋር ግንኙነት ለሌላቸው የተማሪ ቡድኖች ተደርጎላቸው ከሆነ። እነዚህ ሃይማኖት-ነክ ከስርኣተትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎችን  የሚያደርጉ ቡድኖች በት/ቤት የዓመት መፅሄት ትምህርት ከሚሰጥበት ርእስ ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ከስርዓተትምህርት ውጭ በሚንቀሳቀሱ ቡድኖች ሰክሽን ሊካተቱ ይችላሉ።

ሃይማኖት-ነክ ቡድኖች ኣልፎ ኣልፎ ከውጭ አዋቂዎች ወይም የሃይማኖት መሪዎችን ከስርዓተ ትምህርት ውጭ መጋበዝ ይችላሉ። ቢሆንም፣ በት/ቤቱ ተማሪዎች ያልሆኑ ግለሰቦች በተማሪ በተመሩ ከስርኣተትምህርት ውጭ ቡድኖች ፀሎቶች ወይም ሌሎች ሀይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችን ዘወትር መምራት፣ መከታተል፣ ወይም መቆጣጠር ኣይችሉም።

በተማሪ-የሚመሩ ቡድኖች፣ ሃይማኖታዊም ይሁኑ ኢሃይማኖታዊ፣ ኣካላዊ ጥቃት ወይም ጥላቻ የሚያራምዱ፣ በህገ-ወጥ እንቅስቃሴ የሚሳተፉ፣ ትርጉም የለሽ ረብሻ በት/ቤት የሚቀሰቅሱ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ፀረ-አድልዎ መመርያዎችን የሚጥሱ፣ ወይም በት/ቤት አካባቢ የሌሎችን መብቶች የሚደፍሩ ከሆነ MCPS በት/ቤቶች እንዲሰበሰቡ ኣይፈቀድላቸውም። የሆነ ሆኖ፣ የኣወዛጋቢና ውስብስብ ማህበራዊና ህጋዊ ጉዳዮችን ውይይት በማካተታቸው ምክንያት ብቻ ት/ቤቶች ተማሪዎችን ቡድኖች ከመመስረት መከልከል የለባቸውም።

ተማሪዎች በቅድመ- ወይም ድህረ-ትምህርት ክውነቶች ሃይማኖታዊ ይዘት ባላቸው ክውነቶች ልክ በሌሎች ከስርአተትምህርት ጋር ባልተያያዙ በት/ቤት ግቢ እንቅስቃሴዎች እንደሚደረገው መሳተፍ ይችላሉ።

## የሃይማኖታዊ ድርጅቶች ንብረት በሆኑ መገልገያዎች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አጠቃቀም

ሃይማኖታዊ ያልሆነ አማራጭ ቦታ ማግኘት የሚቻል ከሆነ ለእንቅስቃሴ ወይም ለሆነ ተግባር ተቀባይነት ባለው ደረጃ ተስማሚ መድረክ ሆኖ እያለ የሃይማኖታዊ ድርጅት ንብረት በሆነ ወይም በእነርሱ ኃላፊነት በሚንቀሳቀሱ መገልገያዎች ላይ ለት/ቤት-ነክ እንቅስቃሴዎች ወይም ተግባሮች ት/ቤቶች እንደማይጠቀሙበት ተማሪዎችና ወላጆቻቸው/አስዳጊዎቻቸው ማወቅ ይገባቸዋል። ት/ቤቶች ማንኛውንም የግል ሃይማኖታዊ መገልገያን የዚህ አይነቱ መገልገያ ከማንም የሃይማኖት አስተምህሮዎች ገፅታ ጋር በመያያዙ በመመስረት ብቻ አይመርጡም ወይም ውድቅ አያደርጉም፤ እንዲያውም፣ እነዚህን አገልግሎቶች ለመምረጥ MCPS ቅርበት፣ የመገልገያው ተስማሚነት ለሚፈለገው አገልግሎት፣ ጤናና ደህንነት፣ ተመጣጣኝ ወጪ፣ እና መዳረሻን የመሳሰሉ ከሃይማኖት ነፃ የሆኑ መስፈርቶች አገልግሎት ላይ ይውላሉ።

ት/ቤት-ነክ የሆነ መገልገያ ወይም ተግባር በአንድ ሃይማኖታዊ ድርጅት ንብረት በሆነ ወይም በሚንቀሳቀስ መገልገያ ውስጥ ከተካሄደ፣ ተማሪዎችና ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው ት/ቤቱ መገልገያውን ከሃይማኖት ነፃ ለሆነ አላማ እንደሚጠቀምበት ይለያል፣ በተቻለ መጠን ደግሞ፣ ት/ቤት-ነክ እንቅስቃሴዎች በሚካሄዱበት ወቅት የሃይማኖት ምስሎች፣ መልእክቶች፣ ወይም የኪነጥበብ ስራዎች በክፍሎቹ እንደማይታዩ ያረጋግጣል። በተጨማሪ፣ የት/ቤት-ነክ እንቅስቃሴ ወይም ተግባር ተሳታፊዎች በሚያልፉባቸው አካባቢዎች የጎሉ ሃይማኖታዊ ምስሎች፣ መልእክቶች ወይም ኪነጥበባት መጋለጥን ለማስወገድ ወይም ለማሳነስ የተቻለ እርምጃ ሁሉ ይወሰዳል።

## በት/ቤቶችና በእምነት ማህበረሰቦች መካከል የሚከናወን ህብረት

ልክ ከቢዝነሶችና ሌሎች የማህበረሰብና የሲቪል ቡድኖች ጋር እንደሚያደርገው፣ MCPS ከእምነት ህብረተሰብ ጋር ሽርክናዎችን ለመንከባከብና ለማዳበር ይሰራል። እያንዳንዱ የህብረተሰብ አካል ትምህርትን ለመደገፍ ሲሰባሰብ ተማሪዎችና ት/ቤቶች እጅግ በጣም ያተርፋሉ።

ማንኛውም የእምነት ማህበረሰብ ሽርክና ፕሮግራም የጠራ አለማዊ/መንፈሳዊ ያልሆነ አላማ እንዲኖረው ያስፈልጋል እናም ሃይማኖትን ማራመድ ወይም ማገድ የለበትም። ተማሪዎች እንዲሳተፉ የሚመረጡት፣ በማናቸውም ኃይማኖታዊ ቡድን አባልነት፣ወይም ማናቸውንም ኃይማኖታዊ እምነትን ስለተቀበሉ ወይም ስላልተቀበሉ፣ ወይም በማናቸውንም ዓይነት የኃይማኖት እምነት እንቅስቃሴዎች ላይ ለመሳተፍ ፈቃደኞች መሆናቸውና ያለመሆናቸዉን መሠረት በማድረግ አይደለምም።

የእምነት ማህበረሰቦች በጎ-ፈቃደኞች የማንኛውም አጋርነት ዓላማ በተፈጥሮ ትምህርታዊና ኢሀይማኖታዊ/ዓለማዊ መሆኑን፣ እናም በጎ-ፈቃደኞች በመጀመሪያው የህገ መንግሥት ማሻሻያ አዋጅ/First Amendment የተማሪዎችን መብቶች ማክበር እንዳለባቸው ማወቅ ይገባቸዋል። በት/ቤት ስፖንሰር በሚደረግ እንቅስቃሴ በመምራት ወይም በመሳተፍ ላይ በሚገኙበት ወቅት በጎ-ፈቃደኞች ወይም ተሳታፊዎች በማንኛውም የእምነት ማህበረሰብ የጋራ ፕሮግራም ስለ ሃይማኖታቸው ለተማሪዎች መስበክ ወይም በሃይማኖታዊ አምልኮ መሳተፍ አይችሉም። የእምነት ማህበረሰብ ሽርክና ፕሮግራም በጎ-ፈቃደኞች እና ተሳታፊዎች በሌሎች የማህበረሰብ ድርጅቶች እንደሚደረገው ሁሉ MCPS የመረጃያዊ ቁሳቁሶች ስርጭት ህጎችን መከተል አለባቸው።

## ■ ለሁሉም የመከባበር ባህልን ማዳበር/ማሳደግ

በሁሉም የ MCPS ማህበረሰብ መካከል የመከባበር ባህል እንዲዳብር ለመርዳት እነዚህ መመርያዎች ተዘጋጅተዋል። በማህበረሰቦች ውስጥ ካለው ከፍተኛ ብዝሃነት/diversity ጋር፣ የመከባበር፣ መቀባበልና የመቻቻል ባህል ሲኖር እርስ-በርሳችን የምንማረው በጣም ብዙ ይኖራል። ት/ቤቶቻችን ደጋፊና ምቹ የመማር አካባቢ ለመፍጠር ይሰራሉ፣ እናም ወላጆች/አሳዳጊዎች ከመምህራንና ከአስተዳዳሪዎች ጋር የቤተሰቦቻቸውን ፍላጎቶች ሃይማኖታዊ እምነቶቻቸውንና ልምዶቻቸውን ደጋፊ እንደመሆናቸው ለመገንዘብ በቅርብ እንዲሰሩ ይበረታታሉ።

አወንታዊና ክቡር የሆኑ ት/ቤቶችን ለመፍጠር ከምናደርገው ጥረት አካል፣ ተማሪዎች ለሰላማዊ የመማርያ አካባቢ መብት አላቸው፣ ከማንኛውም አይነት ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ እና ከማስፈራራት ነፃ የሆነ የተማሪው/ዋ ሃቀኛ ወይም የሚገመቱ የግል ባህሪዎች ላይ የተመሰረተ ማስፈራራት ፣ ሃይማኖትን ጨምሮ ። በተጨማሪም፥ ቦርዱ ቋንቋን እና/ወይም ጥላቻን የሚያራምዱ እና በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክቱ ሥራዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ጫና/መሰናክል ሊያስከትሉ የሚችሉ ምስሎችን እና ምልክቶችን ማሳየትን ይከለክላል። አመፅ የደረሰባቸው ተማሪዎች፣ አመፅ የሚፈፅሙ ተማሪዎች፣ እና አመፅ ቆመው የሚመለከቱ ተማሪዎች ለጤና፣ ደህንነት እና ለትምህርት አሉታዊ ውጤቶች አደጋዎች የተጋለጡ ናቸው። ማሸማቀቅን፣ ወከባን፣ ወይም ማስፈራራትን ለመከላከል እና ሲፈፀም በውጤታማነት ጣልቃ ለመግባት፣ እንዲሁም ማሸማቀቅ፣ ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት ዘገባ በሚያቀርቡ ላይ የበቀል እርምጃ የሚፈፅሙትን ለመከላከል MCPS ስርአት-አቀፍ አቅርቦት ተልሞ ተግባራዊ አድርጓል። እንደነዚህ ያሉ ድርጊቶችን ሪፖርት ለማድረግ፣ ተማሪዎች ወይም ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው ማንኛውንም ችግር ለመፍታት MCPS ቅጽ 230-35፣ ጉልበተኝነትን፣ ትንኮሳን፣ ወይም ማስፈራሪትን ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ለመሙላት ከትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ጋር መስራት አለባቸው። በኦንላይን የሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ (ተመራጭ ይሆናል) እና በወረቀት ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ እዚህ ይገኛል ። www.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/detail.aspx? formNumber=230-35&catID=1&subCatId=44

ከቦርድ ፖሊሲ COA፣ የተማሪ ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም ጋር በተገናዘበ መልኩ MCPS ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት ቤት አካባቢዎችን እና የስራ ቦታዎችን ለመንከባከብ የባህሪ ግምገማ ላይ በመመስረት ተገቢውን የመከላከል ወይም የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስጋ ባህርይ ግምገማ ሥርአት አብጅቷል። ሁሉም ልጆች አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ስነልቦናዊ ደህንነታቸውን የሚደግፍ ሠላማዊና የሚያበለጽግ የትምህርት ቤት አውድ እንዲኖራቸው ይገባል። ለሁሉም ተማሪዎች የመማር እድልን ለማስፋት እንደነዚህ አይነት ሠላማዊ እና ምቹ አካባቢዎች ወሳኝ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። ከቦርድ ፖሊሲ ACA አድሎአዊነት የሌለው፣ ፍትሃዊነት እና የብቃት ባህል ጋር የሚጣጣሙ የትምህርት ቤት ደህንነት እርምጃዎች በተማሪዎች እውነተኛ ወይም በይሆናል የግል ባህሪያቸው ተመስርቶ በአድሎ መተግበር የለበትም። በትምህርት ቤት ደረጃ አስጊ ባህርይን የመከታተልና የማጥናት ሒደት ተግባራዊ

የማድረግ ሃላፊነት ያለባቸው ሠራተኞች ውስጥ ለውስጥ የሚደረግ ለአንድ ወገን ማድላትን ለመረዳት እንዲችሉ እና የብዝሃነት ግንዛቤን እንዲያዳብሩ-እንዲያራምዱ ሠልጥነዋል።

ማጣቀሻዎች፡-

የቦርድ ፖሊሲ ACA  አድሎ የሌለበት፣ ሚዛናዊነትና ፍትኃዊነት፣  እና ባህላዊ ብቃት -

የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ COA፣  የተማሪ ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም/Student Well-being and School Safety

የቦርድ ፖሊሲ JHF  ዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ወይም ጥቃት

MCPS ደንብ COA-RA ፣  የሚያሰጋ ባህሪ ግምገማ   ።

MCPS ደንብ JHF-RA፣ ተማሪን በጉልበት፥ በሥልጣን ተጠቅሞ ማጥቃት፥ ጭቆና፥ ትንኮሳ፥ ወይም ማስፈራራት

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Well-being<br>Office of Well-being, Learning and Achievement<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-5630<br>504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

**ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

ህትመት፡- Department of Materials Management for the Office of Strategic Initiatives

0833.23ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 10/23 • NP